| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ድርሰት ። |
| ርእስ ፤ | "ፈደልን ፡ የጠነቀቁ ፡ መጠቁ ። " |
| ደራሲ ፤ | ወሌ ፡ ነጋ ። |
| ዕለት ፤ | ሚያዝያ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2011.001 |
| ማስታወሻ ፤ | የግል ፡ አስተያየት ። |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ፈደልን ፡ የጠነቀቁ ፡ መጠቁ ።

ወሌ ፡ ነጋ ።

*"ለሰው ፡ መስታዎቱ ፡ ሰው ፡ ነው"* ፡ ይባላል ። የሰው ፡ ልጅ ፡ ማኅበራዊ ፡ ፍጥረት ፡ ነውና ፥ ለሰው ፡ ዐይን ፡ ዋጋን ፡ ይሰጣል ። ባቀራረቡ ፡ ሰውን ፡ እንዳያስከፋ ፥ አፍኣዊ ፡ ግጻዌውን ፡ ወይም ፡ ክሥተቱን ፡ አስቀድሞ ፡ ያስተካክላል ። መስታዎት ፥ ያውም ፡ የዘመናችን ፥ ከጥራቱ ፡ የተነሣ ፥ ገጽታችንን ፡ ፍንትው ፡ አድርጎ ፡ ስለሚያሳየን ፥ አንዳች ፡ ጕድፍ ፡ ወይ ፡ ስሓ ፡ ቢኖር ፡ እናስወግድበት ፡ ዘንድ ፥ ጧት ፡ ማታ ፡ እንጐበኘዋለን ። የመስታዎት ፡ ዋጋው ፡ እንግዲህ ፡ ጥራቱ ፡ ነው ። የመስታዎትን ፡ አብነት ፡ በመከተል ፥ ***"ለሰው ፡ መስታዎቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው"*** ፡ ስል ፡ እላይ ፡ የጠቀስኹትን ፡ አባባል ፡ ለወጥ ፡ ላድርገውና ፡ አንድ ፡ አፍታ ፡ ልተንትነው ።

ደራሲ ፡ በመጽሐፉ ፡ ራሱን ፣ አካባቢውን ፣ ኅብረሰቡን ፣ ዓለሙን ፡ በጠቅላላው ፡ እንደ ፡ መስታዎት ፡ ያይበታል ። አንባቢም ፥ ተራውን ፥ በመጽሐፉ ፡ አማካይነት ፡ ደራሲውን ፣ አካባቢውን ፣ ኅብረሰቡን ፣ ራሱንም ፡ ያይበታል ፤ ምናልባትም ፥ ደራሲው ፡ ራሱ ፡ ባላየበት ፡ መንገድ ፡ አንባቢው ፡ ባንድያ ፡ እይታው ፡ በተለየ ፡ ያይበታል ። ለዚህ ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ የመጽሐፉ ፡ ጥራት ፡ ይህን ፡ የደራሲንና ፡ ያንባቢን ፡ ሱታፌ ፡ ይወስነዋል ።

የመጽሐፍ ፡ ጥራት ፡ ቢያንስ ፡ ሦስት ፡ መለኪያዎች ፡ አሉት ፤

- አንደኛ ፥ ፈደል ፡ ጥንቀቃው ፤
- ኹለተኛ ፥ አገባብ ፡ ጥንቀቃው ፤
- ሦስተኛ ፥ ያገላለጽ ፡ ትኽክልነቱ ።

በክፍል ፡ አንድ ፥ የዘመናችንን ፡ ያማርኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ዝልጉስነት ፡ በወፍ ፡ በረር ፡ አሳያለኹ ። በኹለተኛው ፡ ክፍል ፥ ከእነዚህ ፡ ሦስት ፡ ነጥቦች ፡ ውስጥ ፡ በመዠመሪያው ፡ በፈደል ፡ ጥንቀቃ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ በማተኰር ፥ ፈደል ፡ ጥንቀቃ ፡ ለሀገራዊ ፡ ልማት ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ መሠረታዊ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስታውሼ ፥ በሦስተኛውና ፡ መጨረሻው ፡ ክፍል ፥ ፈደልን ፡ አለመጠንቀቅ ፡ በሀገራዊ ፡ ህልውናችን ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ጕዳት ፡ እንደሚያስከትል ፡ አስገንዝቤ ፥ "ምን ፡ ይደረግ ፧ " ፡ ለሚለው ፡ ጥያቄ ፡ የመፍትሔ ፡ ሐሳቦችን ፡ አመልክቼ ፡ እደመድማለኹ ።

## 1 ፤ የመጽሐፍ ፡ ጥራት ፡ በገቢር ።

ሰሞኑን ፥ በኢትዮጵያ ፡ ላ 12 ኛ ፡ ክፍል ፡ ያማርኛ ፡ መማሪያ ፡ የተዘጋጀን ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ አግኝቼ ፡ ተመልክቼ ፡ ነበር ። ቢነግሩኝ ፡ ለማመን ፡ የሚቸግረኝን ፡ የተበላሸ ፡ ኹኔታ ፡ በዐይኔ ፡ ስላየኹ ፥ እጅግ ፡ አዘንኩ ፤ ይህን ፡ ጽሑፍ ፡ ለመጻፍም ፡ ከገፋፉኝ ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ ኾነ ።

### 1.1 ፤ ፈደል ፡ ጥንቀቃ ።

በመጽሐፉ ፡ በመዠመሪያው ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ የሰፈረውን ፡ አንድ ፡ መነሻ ፡ (paragraph) ፥ በተጻፈበት ፡ ኹኔታ ፥ የተሳሳቱት ፡ ፈደሎቹን ፡ በብጫ ፡ መደብ ፡ በማቅለምና ፥ ከራስጌያቸው ፡ ማረሚያውን ፡ በማመልከት ፡ ለጥቆ ፡ ጠቅሼዋለኹ ፦

> *«የዚህ መጽሐፍ ዲዛይን ህትመትና ስርጭት ማከናወኛ ገንዘብ የተገኘው በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት (GEQIP) አማካኝነት ነው ። የፕሮጀክቱ ዋና ዓላማ በአገሪቱ በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከ 1 ኛ–12 ኛ የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል ነው ። »*

የተጠቀሰው ፡ ዐጪር ፡ ጽሑፍ ፡ በጠቅላላው ፡ ኹለት ፡ አረፍተ ፡ ነገሮች ፡ አሉት ፤ እነዚህም ፡ በድምሩ ፡ 131 ፡ ፈደሎችና ፡ 31 ፡ ቃላት ፡ አሏቸው ። ከ 31ዱ ፡ ቃላት ፡ 5 ቱ ፡ የፈደል ፡ ስሕተት ፡ አለባቸው ፤ በሌላ ፡ አነጋገር ፥ ከ 6 ፡ ቃላት ፡ አንዱ ፡ ስሑት ፡ ነው ። ይህ ፡ ባንድ ፡ መነሻ ፡ የታየ ፡ የፈደል ፡ ስሕተት ፡ መጠን ፥ ባንድ ፡ ገጽ ፡ ሲሰላ ፥ በግምት ፡ ከ 30 ፡ እስከ ፡ 40 ፡ የተሳሳቱ ፡ ቃላት ፡ በያንዳንዱ ፡ ገጽ ፡ ይገኛሉ ።

እላይ ፡ የተጠቈሙትን ፡ የፈደል ፡ ስሕተቶች ፡ ዐርመናቸው ፦

> *«የዚህ መጽሐፍ ዲዛይን ኅትመትና ሥርጭት*


©አ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

*ማከናወኛ ገንዘብ የተገኘው በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት (GEQIP) አማካይነት ነው ። የፕሮጀክቱ ዋና ዐላማ በአገሪቱ በሚገኙ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ከ 1ኛ–12ኛ የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል ነው ። » ፥*

ወዳገባብ ፡ ዕርማት ፡ እንሸጋገር ።

**1.2 ፤ አገባብ ፡ ጥንቀቃ ።**

ፊደሉ ፡ የታረመለትን ፡ ጽሑፍ ፡ ባገባብ ፡ ረገድ ፡ ስንፈትሸው ፥ በብጫ ፡ መደብ ፣ ባረንጓዴ ፡ ቀለም ፡ የተመለከቱትን ፡ ዕርማቶች ፡ እናክላለን ፦

*«የዚህ መጽሐፍ የዲዛይን ፣ የኅትመትና የሥርጭት ማከናወኛ ገንዘብ የተገኘው በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት (GEQIP) አማካይነት ነው ። የፕሮጀክቱ ዋና ዐላማ በአገሪቱ በሚገኙ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ከ 1ኛ–12ኛ የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል ነው ። »*

ከኹለት ፡ አረፍተ ፡ ነገሮች ፡ ወስጥ ፡ አንዱ ፡ ያገባብ ፡ ስሕተቶች ፡ አሉበት ፤ 50% ፡ ማለት ፡ ነው ።

**1.3 ፤ ያገላለጽ ፡ ትኽክልነት ።**

ያገላለጽ ፡ ወይም ፡ የትርጕም ፡ ትኽክልነት ፡ የሚገኘው ፥ የታሰበውን ፡ ጕዳይ ፥ በሚነገርበት ፡ ቋንቋ ፡ አሟልቶና ፡ አስተካክሎ ፡ መንገር ፡ ማለት ፡ ነው ። አኹንም ፥ የጥቅሱን ፡ ያገላለጽ ፡ ትኽክልነት ፡ እንፈትሸውና ፦

*«የዚህ መጽሐፍ የዲዛይን ፣ የኅትመትና የሥርጭት ማከናወኛ ገንዘብ የተገኘው በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት (GEQIP) አማካይነት ነው ። የፕሮጀክቱ ዋና ዐላማ በአገሪቱ በሚገኙ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ከ 1ኛ–12ኛ የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል ነው ። »*

ኹለቱም ፡ አረፍተ ፡ ነገሮች ፡ ያገላለጽ ፡ ሕጸጽ ፡ አለባቸው ። ሐሳቡ ፡ የሚገለጽበት ፡ ቋንቋ ፡ ዐማርኛ ፡ ሳለ ፥ በማያስፈልጉ ፡ የፈረንጅኛ ፡ ቃላት ፡ ጭምር ፡ ተገልጧል ። ቃላቱ ፡ ባማርኛ ፡ ሊነገር ፡ የማይቻልን ፡ ሐሳብ ፡ ለመግለጽ ፡ ውለው ፡ ቢኾን ፥ አደራረጉ ፡ ስሕተት ፡ ባልኾነ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥

"ዲዛይን"ን ፡ "ዝግጅት" ፣ "ፕሮጀክት"ን ፡ "ዕቅድ" ፡ ማለት ፡ እየተቻለ ፥ በፈረንጅኛ ፡ መግለጹ ፥ አንድም ፡ ስንፍናን ፥ አንድም ፡ አለመገንዘብን ፡ ያመለክታል ።

የጥቅሱን ፡ ያገላለጽ ፡ ትኽክልነት ፡ እናሻሽለውና ፦

*«የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የዝግጅት ፣ የኅትመትና ፡ የሥርጭት ፡ ማከናወኛ ፡ ገንዘብ ፡ የተገኘው ፡ በአጠቃላይ የትምህርት ፡ ጥራት ፡ ማሻሻያ ፡ ዕቅድ ፡ (ት.ጥ.ማ.ዕ. | GEQIP) ፡ አማካይነት ፡ ነው ። የዕቅዱ ፡ ዋና ዐላማ ፡ በአገሪቱ ፡ በሚገኙ ፡ የመንግሥት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ከ 1ኛ–12ኛ ፡ የሚሰጠውን ፡ የትምህርት ፡ ጥራት ፡ ማሻሻል ነው ። »*

ስንፍናም ፡ ቸልተኝነትም ፡ ለትምህርት ፡ መጽሐፍ ፡ ዝግጅት ፡ ፈጽሞ ፡ አይገቡም ፤ አርኣያነታቸው ፡ አፍራሽ ፡ ይኾናል ። ይህንም ፡ የሚቀጥለው ፡ ክፍል ፡ ባጪሩ ፡ ያሳየናል ።

**2 ፤ ፊደልን ፡ ያልጠነቀቁ ፥ ወደቁ ።**

ዛሬ ፥ ኢትዮጵያዊ ፡ በሀገራዊነቱ ፡ ምክንያት ፡ ከገዛ ፡ ሀገሩ ፡ በሚፈናቀልበት ፡ ሰዓት ፥ ከቶ ፡ ስለፊደል ፡ ጥንቀቃ ፡ ማተቱ ፡ ቅንጦት ፡ አይኾብንምን ፥ ብላችኹ ፡ ለምትጠይቁ ፥ የሚከተለው ፡ በቂ ፡ መልስ ፡ እንደሚኾንላችኹ ፡ አምናለኹ ።

ስለፊደል ፡ ጥንቀቃ ፡ ለማወቅ ፡ ፈረንጅ ፡ አገር ፡ መኼድ ፡ አያሻንም ፤ ኢትዮጵያም ፡ ብትኾን ፥ የዛሬን ፡ አያድርገውና ፥ በቀለም ፡ ታሪኳ ፥ እንደ ፡ መጽሐፈ ፡ ሔኖክ ፡ ያሉትን ፥ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ የጠፉትን ፡ ጥንታውያን ፡ መጻሕፍት ፡ አስተካክላ ፡ እየገለበጠችና ፡ በጥንቃቄ ፡ እየያዘች ፡ እዘመናችን ፡ አድርሳለች ። በዚህ ፡ ረገድ ፥ የመዠመሪያዋ ፡ ተመስጋኝ ፡ **የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን** ፡ ናት ። መንግሥትም ፡ ቢኾን ፥ እንደ ፡ ዐፄ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብና ፡ እንደ ፡ ዐፄ ፡ በካፋ ፡ ባሉ ፡ ተቈርቋሪዎች ፡ መሪነት ፥ ስለ ፡ ቋንቋና ፡ ስለ ፡ ጽሑፍ ፡ ጥራት ፡ ታላቅ ፡ ውለታን ፡ ውሏል ። በተለይ ፡ በዐፄ ፡ በካፋ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፥ ደብተራዎችና ፡ የመጽሐፍ ፡ ገልባጮች ፡ በጥብቅ ፡ ቍጥጥር ፡ ይሠሩ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ይነገራል ። አንድ ፡ ገልባጭ ፥ ፊደልን ፡ የማይጠነቅቅ ፡ ኾኖ ፥ በተደጋጋሚ ፡ የሚሰጠውን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ችላ ፡ ቢል ፥ እጅ ፡ እስከ ፡ መቌረጥ ፡ የሚያደርስ ፡ ቅጣትን ፡ ይቀጣ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ይተረካል ። ቅጣቱ ፡ በእውን ፡ ይፈጸም ፡ አይፈጸም ፥ ማረጋገጫ ፡ ባይኖርም ፥ የሥርዐቱ ፡ ጥብቅነት ፡ ምን ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ያኽል ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ያሳየናል ።

ይህ ፡ ዅሉ ፡ ተረስቶ ፥ ዛሬ ፥ በየመጽሐፉ ፡ ፊደልና ፡ አገባብ ፡ እንዲህ ፡ እጅና ፡ እግራቸው ፡ ተሰባብሮ ፡ ማየቱ ፤ ከዚህም ፡ የባሰ ፥ የወጣቶችን ፡ አእምሮ ፡ የሚያደንዝ ፡ አጥፊ ፡ ድርጊት ፡ አላንዳች ፡ ሀይ ፡ ባይ ፡ በሕዝብ ፡ ገንዘብ ፡ ሲፈጸም ፡ ማየቱ ፡ ያስቈጣል ፥ ያሳዝናል ።

*"ውድቀቱ ፡ ነው ፡ የቀደመው ፡ ወይስ ፡ ፊደል ፡ አለመጠንቀቁ ፧ "* ፡ የሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ያከራክረን ፡ ይኾናል ፤ የማያከራክረን ፡ ግን ፡ አንድ ፡ እውነት ፡ አለ ፦ ***ከበለጸጉት ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ አንድም ፡ ፊደልን ፡ የማይጠነቀቅ ፡ አይገኝም!***

ፊደል ፡ ጥንቀቃ ፡ የልማት ፡ አንዱ ፡ ተሸካሚ ፡ ዐምድ ፡ ነው ። ርሱ ፡ ቢናጋ ፥ ልማቱ ፡ በጠቅላላው ፡ በቅጽበት ፡ ይናዳል!

እስቲ ፡ አንድ ፡ አፍታ ፡ ዐስቡት ፦ *"ከዛሬ ፡ ዠምሮ ፡ ፊደል ፡ ጥንቀቃ ፡ ይቅር"* ፡ የሚል ፡ ዐዋጅ ፡ በመላ ፡ ዓለም ፡ ቢታወጅና ፡ ይህም ፡ ቢፈጸም ፥ ወዲያዉኑ ፥ የልማት ፡ በረከቶች ፡ የምንላቸው ፡ የሥጋዊ ፡ ምቾታችንና ፡ ድሎታችን ፡ መሠረቶች ፡ የኾኑት ፡ የሥልጣኔ ፡ ውጤቶች ፡ ዅሉ ፡ (የውሃ ፣ የኤሌክትሪክ ፣ የመጓጓዣ ፣ የስልክ ፣ የሕክምና ፣ ያስተዳደር ፣ የጽዳት ፣ የንግድ ፣ የገንዘብ ፡ ቤት ፣ የጸጥታ ፣ የመገናኛ ፣ የማወራኛ ፣ ወዘተርፈ ፡ አገልግሎቶች ፡ ዅሉ) ፡ በዚያው ፡ ቅጽበት ፡ አንድጋ ፡ ተሸመድምደው ፡ ሲንኰታኰቱ ፥ ዓለማችን ፡ በከፋ ፡ ነውጥ ፡ ወደጨለማ ፡ ዘመን ፡ ትሸቀነጠራለች ።

ፊደል ፡ ጥንቀቃ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ለልማት ፡ መሠረታዊ ፡ ነው ። ይህም ፡ በመኾኑ ፥ የበለጸጉት ፡ አገሮች ፡ ዅሉ ፥ በሥርዐተ ፡ ትምህርታቸው ፥ ለፊደል ፡ ጥንቀቃ ፡ ቀዳሚውን ፡ ቦታ ፡ ሰጥተው ፥ ተማሪዎቻቸው ፥ ገና ፡ ያንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርታችውን ፡ ሲያጠናቅቁ ፥ በፊደል ፡ ጥንቀቃ ፡ ረገድ ፥ መደበኛ ፡ ልምድን ፡ ያገኛሉ ። እስካ 12 ኛ ፡ ክፍል ፡ መማር ፡ ደግሞ ፡ ግዴታቸው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በቂ ፡ የፊደል ፡ ጥንቀቃ ፡ ልምድን ፡ ያገኛሉ ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፥ በማንኛውም ፡ የሚያ ፡ መስክ ፡ የሚደረጉ ፡ መጻጻፎች ፣ የሚወጡ ፡ ደንቦችና ፡ መመሪያዎች ፣ የሚታተሙ ፡ መጽሐፎች ፣ የሚመዘገቡ ፡ ያዳዲስ ፡ ቃላት ፡ አጻጻፎችም ፡ ጭምር ፥ አላንዳች ፡ በቀርታ ፥ ፊደላቸው ፡ ተጠንቅቆ ፡ ይጻፋሉ ። ከዚህ ፡ አሠራር ፡ አፈነግጣለኹ ፡ የሚል ፡ ሠራተኛም ፥ ከሥራ ፡ መባረሩን ፡ የፈለገ ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፥ አይገኝም ።

**3 ፤ *መንግሥት* ፡ ሲቀና ፥ *ፊደል* ፡ ይቀና ፤ *ፊደል* ፡ ሲቀና ፥ *መንግሥት* ፡ ይቀና ።**

*"ቋንቋ ፡ የሚስፋፋ ፡ በመንግሥት ፡ ነው"* ፡ ብለዋል ፡ አለቃ ፡ ደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፡ (1893–1977 ፡ ዓ.ም.) ። ሰው ፡ በግሉ ፡ በሚጣጣርበት ፡ ኹኔታ ፥ ራሱንና ፡ የቅርብ ፡ አካባቢውን ፡ ይለውጥ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፥ ሰፊውን ፡ ኅብረሰብ ፡ አያዳርስም ። ይህን ፡ ሊፈጽሙ ፡ የሚችሉ ፡ እንደ ፡ ቤተ ፡ እምነቶችና ፡ እንደ ፡ መንግሥት ፡ ያሉ ፡ ሀገራዊ ፡ መሠረት ፡ ያላቸው ፡ ተቋማት ፡ ናቸው ። በተለይ ፡ መንግሥት ፥ በዘመናችን ፥ አንድያው ፡ የዘመናዊነት ፡ አረማማጅ ፡ ኀይል ፡ ስለ ፡ ኾነና ፥ ሥራውም ፡ በዐቅድ ፡ ከመመራቱ ፡ ጋራ ፥ በሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ጸንቶ ፥ በመላው ፡ መንግሥታዊ ፡ ኀይልና ፡ ተቋም ፡ ስለሚከናወን ፥ የሕዝብን ፡ ውዴታ ፡ እያገኘ ፥ በሠመረ ፡ መንገድ ፡ ሥራውን ፡ ይፈጽመዋል ።

የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ያለው ፡ ሕጋዊ ፡ መንግሥት ፥ ለሠየመው ፡ ሕዝብ ፡ ተገዥ ፡ የኾነውን ፡ ያኽል ፥ ሠያሚውም ፡ ሕዝብ ፡ ተራውን ፡ ስለሚገዛለት ፥ ኹለቱም ፡ የልማትን ፡ ጥቅም ፡ ሲሹ ፥ ፊደል ፡ ጥንቀቃን ፡ ጨምሮ ፥ ልማት ፡ የሚጠይቃቸውን ፡ ግዴታዎች ፡ ዅሉ ፡ ለማሟላት ፡ ይሰላሉ ። የዘሩትን ፡ ማጨድ ፡ አግባብ ፡ ነውና ፥ ይህ ፡ ቀና ፡ አካኼድ ፡ ተራውን ፡ ለመንግሥትና ፡ ለሕዝቡ ፡ የተመኟቸውን ፡ የልማት ፡ ፍሬዎች ፡ ያጐናፍርላቸዋል ።

**3.1 ፤ ኢትዮጵያ ፡ ዛሬ ፡ የምትገኝበት ፡ ኹኔታ ።**

እላይ ፡ የጠቀስኹት ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ በኢትዮጵያ ፡ አለመኖሩን ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ ራሱ ፡ እሥልጣኑ ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ የወጣው ፡ ኀይልም ፡ ያውቀዋል ። **ኢትዮጵያ ፥ ዛሬ ፥ ተገቢ ፡ ሕገ ፡ *መንግሥትም* ፣ ተገቢ ፡ *መንግሥትም* ፡ የላት ።** በዚህ ፡ ኹኔታ ፥ ፊደል ፡ ጥንቀቃ ፡ ቀርቶ ፥ ሕግ ፡ ጥንቀቃም ፡ አይኖርም ። ጧት ፡ ማታ ፡ የሚቀሽልን ፡ *"ባለኹለት ፡ አኃዝ"* ፡ እድገትም ፥ የዋጋ ፡ ንረትን ፡ እንጂ ፥ የሀብት ፡ ንረትን ፡ አያመለክትም ። ልማቱ ፡ ቀርቶ ፥ ሰው ፡ ከገዛ ፡ ሀገሩ ፡ መፈናቀሉ ፡ ባበቃ ። በዚህ ፡ ኹኔታ ፡ ስለፊደል ፡ ጥንቀቃ ፡ መሻሻል ፥ መናገር ፡ ቀርቶ ፥ ማሰብም ፡ ይቀፋል ። ኾኖም ፥ ሐኪም ፡ በሽተኛን ፡ ሲያክም ፥ የበሽታውን ፡ ምንነት ፡ ለይቶ ፡ ስለ ፡ መድኀኒቱ ፡ ያስባል ፡ እንጂ ፥ በበሽታው ፡ ሠቀቀንና ፡ ሥቅቅታ ፡ መቆጥ ፡ አይገባውም ። መድኀኒቱ ፡ ላይ ፡ እናተኵር ።

**3.2 ፤ ምን ፡ ይደረግ ፧**

*"ያፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ ሀገሮች ፡ ይዋሐዱ ፡ ..."* ፣ *"ኢትዮጵያ ፡ ካማርኛ ፡ ሌላ ፡ ተጨማሪ ፡ የሥራ ፡ ቋንቋ ፡ ያሻታል ፡ ..."* ፣ ወዘተ. ፡ የሚሉ ፡ ሐሳቦች ፡ ዘንድሮ ፡ ከባለጊዜዎቹ ፡ አንደበት ፡ ተደጋግመው ፡ ይሰማሉ ።

ኹኔታው ፡ ፈቅዶ ፥ ያፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ ሀገሮች ፡ ብቻ ፡ ሳይኾኑ ፥ የመላ ፡ አፍሪቃ ፡ ሀገሮችም ፡ ቢዋሐዱ ፡ መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ይደሰትበታል ፤ ምንም ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ። ከኢትዮጵያ ፡ ዠምሮ ፥ ተገቢ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

መንግሥት ፡ የሌላቸው ፡ ሀገሮች ፡ ቢዋሐዱ ፡ ግን ፥ ተስቦ ፡ የታመመን ፡ በሽተኛ ፥ የሳምባ ፡ በሽታ ፡ ከያዘው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ ክፍል ፡ እንደማሳደር ፡ ያለ ፡ በደል ፡ ይኾናል ። እንደዚሁም ፥ ሀገራዊ ፡ ቋንቋችንን ፡ ዐማርኛችንን ፡ በቅጡ ፡ ሳንይዝ ፥ የጎሳ ፡ ቋንቋን ፡ ተጨማሪ ፡ የሥራ ፡ ቋንቋ ፡ እናድርግ ፡ ማለት ፥ ሀገራዊ ፡ ቋንቋችንን ፡ አድክመን ፥ የጎሳ ፡ ቋንቋውንም ፡ ሳንጠቅም ፥ ከ"ኢምፔሪያሊዝም" ፡ ቋንቋዎች ፡ ለበረታው ፡ ላንደኛው ፡ የሀገራዊ ፡ ቋንቋችንን ፡ ቦታ ፡ አሳልፎ ፡ መስጠት ፡ ይኾናል ። ኹኔታችን ፡ ዐጓጕል ፡ ነው ፤ ብዙ ፡ አያቀናጣም ።

ምን ፡ ይደረግ ፦ ለሚለው ፡ ጥያቄ ፥ በኹለት ፡ ረድፍ ፡ እመልሳለኹ ።

በግልና ፡ በማኅበር ፡ ደረጃ ፥ ኢትዮጵያውያን ፡ በያለንበት ፥ ለሀገራዊ ፡ ቋንቋችን ፡ ላማርኛ ፡ መጠበቅና ፡ መዳበር ፡ የምንችለውን ፡ ኹሉ ፡ እናድርግ ። ያማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ዕጣ ፡ ፈንታ ፡ ከመንግሥት ፡ እጅ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ሕዝብ ፡ እጅ ፡ ተመልሶ ፡ ገብቷል ። ሕዝብ ፡ ቋንቋውን ፡ ሊከባከብና ፥ በቋንቋው ፡ ሊበጅበት ፡ ይገባል ። ባገር ፡ ውስጥም ፡ በውጭም ፡ ያሉ ፡ የቀለም ፡ ማኅበራት ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ትልቅ ፡ ሚያን ፡ ሊውሉ ፡ ይችላሉ ።

ይህ ፡ የመዠመሪያ ፡ ረድፍ ፡ ሥራ ፡ ለኹለተኛው ፡ ረድፍ ፡ ሥራ ፡ መጋቢ ፡ ስለሚኾን ፥ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ሊሰጠውና ፥ ጥንቃቄ ፡ ሊደረግለት ፡ ይገባል ። የበኩሌን ፡ አስተዋፅኦ ፡ በ"ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ ነጻ ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ መግበር ፡ አበርክቼያለኹ ። ክለሳ ፡ 1.3 ፡ ሚያዝያ ፡ 30 ፡ ቀን ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ ወጥቷል ። ከመርበቢያው ፡ ከ ፡ awdeqelem.net ፡ በነጻ ፡ ይቀዳል ።

በሀገርና ፡ በሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ ደረጃ ፡ የሚሠራው ፡ የኹለተኛው ፡ ረድፍ ፡ ሥራ ፡ ደግሞ ፥ የሀገራችንና ፡ የሀገራዊ ፡ ቋንቋችን ፡ መጋቢ ፡ የኾነውን ፡ መንግሥታችንን ፡ ባዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ ማቆም ፡ ይኾናል ።

ኢትዮጵያዊ ፡ ኹሉ ፡ ጧት ፡ ማታ ፡ የሚጨነቅለትና ፡ የሚጠበብለት ፡ የሀገር ፡ ትድግና ፡ በነዚህ ፡ ኹለት ፡ ተመጋጋቢ ፡ ረድፎች ፡ ሊውን ፡ (እውን ፡ ሊኾን) ፡ ይችላልና ፥ *"እስቲ ፡ ኹላችኹም ፡ ጂ! ፡ በሉ ፥ ጂ! ፡ በሉ ፨ "*


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።